# <u>በኮቪድ 19 ላይ የተሰጠ መግለጫ</u>

## መጋቢት 6፣2012 ዓ.ም

ኢትዮጵያ የኮሮና ቫይረስ ያለበትን የመጀመሪያውን ሰው መጋቢት 4 2012 ካገኘች በሁዋላ፤ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፡ ከግለሰቡ ጋር ንኪኪ የነበራቸውን ሰዎች ሲከታተል ቆይቶዋል። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር እነዚህን ሰዎች የመለየትና የክትትል ስራ ተጥናክሮ የቀጠለ ሲሆን 117 ሰዎች ተለይተው የቅርብ ክትትል እየተደረገላቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ቫይረሱን ለመለየት የሚያስችል ምርመራ ለማድረግ ናሙና እየተወሰደላቸው ይገኛል።

ከእነዚህ ምርመራ ከተወሰደላቸው እና የቅርብ ንክኪ ካላቸው ግለሰቦች መሃከልም ሶስት ግለሰቦች በዛሬው እለት በኮሮና ቫይረስ መያዛቸውን ማረጋገጥ ተችሎዋል። ከእነዚህ ውስጥም ሁለቱ የ 44 እና የ 47 አመት የጃፓን ዜጋ ሲሆኑ፣ አንደኛው ደግሞ የ 42 አመት ኢትዮጵያዊ ነው። ሁሉም የአዲስ አበባ ውስጥ የሚሰሩ እና ቫይረሱ ከተገኘበት የመጀመሪያው ግለሰብ ጋር የቅርብ ንክኪ የነበራቸው ናቸው።

ባሁኑ ስዓት የመጀመሪያው ታማሚ በጥሩ የጤና ሁኔታ ላይ ሲሆን በለይቶ የህክምና መስጫ ማዕከል የቅርብ የህክምና ክትትል እየተደረገለት ነው።

የበሽታውን ስርጭት ለመከላከል ከምንከተላቸው ቁልፍ መንገዶች አንዱ፤ ቫይረሱ ከተገኘበት ጋር የተገናኙ ሰዎችን ተከታትሎ ማግኘትና የጤና ሁኔታቸውን በቅርብ መከታታል ነው። አሁንም እየተደረገ ያለው ይህ ሲሆን ቫይረሱ ዛሬ የተገኘባቸው ሶስት ግለሰቦችም እንደመጀመሪያው ሁሉ የጤና ክትትል እየተደረገላቸው ሲሆን እስከ አሁን የሚያሰጋ ሁኔታ አልታየባቸውም። በተመሳሳይም ከነዚህ ጋር ግኑኝነት የነበራቸውን ሰዎች የማግኘት ስራ ተጀምሯል።

እንደሚታወቀው የአለም የጤና ድርጅት ባሳሰበው መሰረት ከጥር 20 2012 አመት ምህረት ጀምሮ ብሄራዊ የማህበረሰብ ጤና የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎት መስጫ ማእከል በማቋቋም የመከላከያ ስትራቴጂዎችን ስንቀይስ እና ለሁኔታው ስንዘጋጅ ቆይተናል። የክልል እና የከተማ መስተዳድር ጤና ቢሮዎችም

የኢትዮጵያ መንግስት እና የጤና ሚኒስቴር የበሽታውን ስርጭት ለመቆጣጠር እና በቫይረሱ የተያዙ ሰዎችንም በቶሎ ለይቶ እርምጃ ለመውሰድና የበሽታውን ስርጭት ለማስቆምና ጉዳቱን ለመቀነስ ከተለያዩ አጋሮች ጋር የሚቻለውን ሁሉ እያደረገ መሆኑን እናረጋግጣለን። ህብረተሰቡም ይህንን አውቆ በሁኔታዎች ሳይደናገጥ በተረጋጋ መንፈስ የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የሚችለውን ሁሉ እንዲያደርግ በአክብሮት እንጠይቃለን።

አሁንም ማህበረሰቡ የሚከተሉትን የመከላከያ መንገዶችን ቸላ ሳይል እና ሳይደናገጥ ተግባር ላይ በማዋል፣የበሽታውን ስርጭት ለመግታት የበኩሉን እንዲወጣ እናሳስባለን።

- በበሽታው ከታመሙ ሰዎች ጋር ንክኪ የነበረውና ትኩሳትና ሳል ወይም የመተንፈስ ችግር ካለው ግለሰብ ቢያንስ ሁለት የአዋቂ እርምጃ ርቀት ያህል መራቅ፣
- እጅዎን በአግባቡ ሳይታጠቡ አይንና አፍንጫዎን አለመንካት፣
- ከሰዎችጋር አለመጨባበጥ፣
- እጅን በንጹህ ውሃና ሳሙና አዘውትሮ በመታጠብ፣
- የህመም ስሜት ካልዎት ሰዎች ወደሚበዙባቸው ቦታዎች ባለመሄድ፣
- በሚያነጥሱበት እና በሚያስሉበት ጊዜ አፍንና አፍንጫን በሶፍት ወይም ክንድን በማጠፍ በመሸፈን ወደ ሌሎች እንዳያስተላልፉ ይጠንቀቁ፣ የተጠቀሙበትን ሶፍትና ተመሳሳይ ነገሮች በቆሻሻ ክዳን ባላቸው ማጠራቀሚያ ያስወግዱ፣
- በስራ ቦታ፣በትራንስፖርት እና መኖሪያ ወይም የመኝታ ክፍል መስኮት በመክፈት በቂ አየር እንዲኖር ያድርጉ፣
- መረጃዎችን ከአስተማማኝ ምንጮች ብቻ በመቀበል፣ የተሳሳቱ መረጃዎች የሚያስከትሉትን መደናገር እና ፍርሀት እርሶም ይከላከሉ

በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማግኘት የስልክ መስመራችን 8335 ላይ መደወል እንደሚቻል በዚህ አጋጣሚ እንገልጻለን።

ዶ/ር ሊያ ታደሰ

የጤና ሚኒስትር